**በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት**

የመ.ቁ.237771
ጥቅምት 01/2016 ዓ.ም

**ዳኞች፡- ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)**

**በእውቀት በላይ**

**ተሾመ ሽፈራው**

**መላኩ ካሳዬ**

**ነፃነት ተገኝ**

**አመልካች፡ አናህማ ትሬዲንግ ኃላ/የተ/የግ/ማ - ጠ. አቶ አበበ ማስረሻ ቀረቡ**

**ተጠሪ፡- ኒያላ ኢንሹራስ አ/ማ - የቀረበ የለም**

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

ጉዳዩ ከመድህን ሽፋን ውል ጋር በተያያዘ የቀረበ የመዳረግ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/218634 ላይ ጥቅምት 02/2015 ዓ.ም የከፍተኛ ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የጀመረው በፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ነው፡፡ በፍርድ ቤቱ በተደረገው ክርክር የአሁን ተጠሪ ከሳሽ አመልካች ደግሞ ተከሳሽ ነበሩ፡፡ የተጠሪ ክስ ጭብጥም ከአመልካች ጋር ባደረገው የኢንሹራንስ ውል ንብረትነቱ የአመልካች ለሆነ የሰሌዳ ቁጥር 03-77104 ኢ/ት ተሽከርካሪ የመድህን ሽፋን የሰጠ መሆኑን፤ ይህ የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ የሰሌዳ ቁጥሩ 03-31793 ኢ/ት በሆነ ሌላ የአመልካች ተሽከርካሪ ተገጭቶ ከባድ ጉዳት የደረሰበት መሆኑን፤ አመልካች በፌዴራል ከፍተኛ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ፍርድ ቤት በመ/ቁ/236524 በተጠሪ ላይ ክስ ሲያቀርብ በተጠሪ በኩል የማቻቻል ጥያቄ ቢቀርብም ፍርድ ቤቱ የቀረበውን የማቻቻል ጥያቄ በዝምታ አልፎ የመድን ሽፋን የተሰጠው ተሽከርካሪ ሙሉ ውድምት የደረሰበት መሆኑን አረጋግጦ ብር 1,737,312.50 ከእነወለዱ ለአመልካች እንዲከፍል የወሰነበት መሆኑን፤ ተጠሪ ውሳኔውን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ይግባኝ ያቀረበ መሆኑን፤ ፍርድ ቤቱም ተጠሪ የንግድ ህግ ቁጥር 683/1/ በሚያዘው መሰረት በመዳረግ ክስ የማቅረብ መብቱን የጠበቀለት መሆኑን፤ አመልካች የጉዳት አድራሹ ተሽከርካሪ ባለንብረት ሲሆን እንደ ሶስተኛ ወገን የሚቆጠር መሆኑን በመጥቀስ ተጠሪ ለካሳ የከፈለውን ገንዘብ ከእነወለዱ እና ክርክሩ ካስከተለው ወጪ እና ኪሳራ ጋር እንዲተካለት እንዲሁም አመልካች ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ቅሪት አካል ለተጠሪ ያስረከበ ቢሆንም የተሽከርካሪውን ሊብሬ፣ የመንግስት ግብር እና ቀረጥ የተከፈለበትን፤ እዳና እገዳ የሌለበት መሆኑን የሚያረጋግጥ ክሊራንስ እንዲያስረክበው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጠው መልስ ተጠሪ በመዳረግ መብት በተከሳሽ ላይ ክስ ለማቅረብ የሚያስችል መብት ወይም ጥቅም የለውም፤ ጉዳት የደረሰበት ተሽከርካሪም ሆነ ጉዳት ያደረሰው ተሽከርካሪ ሁለቱም የአመልካች ንብረት በመሆናቸው በንግድ ሕግ ቁጥር 683(1)፣ (3) እና በሶስተኛ ወገን መድን ዋስትና አዋጅ ቁጥር 799/2005 መሰረት መድን ገቢው እንደ ሶስተኛ ወገን የሚቆጠር አይደለም፤ መድን ሰጪው መድን ገቢውን ተክቶ ራሱን መድን ገቢውን እንዲክስ መፍቀዱ በራሱ ላይ ክስ እንደማቅረብ የሚቆጠር በመሆኑ ተጠሪ የመዳረግ መብት የለውም፤ ተጠሪ በአንድ በኩል በመዳረግ መብት ካሳ እንዲከፈለው እየጠየቀ በሌላ በኩል ቅሪት አካል ለመሸጥ ቅሪት አካሉን የሚመለከቱ ሰነዶች ለመረከብ የጠየቀው ዳኝነት ተገቢነት የለውም፤ ቅሪት አካሉን የሚመለከቱ ሰነዶችን ለመረከብ መጠየቅ የሚችለው የካሳ ክፍያ ጥያቄ ከሌለው ብቻ ነው፤ የሰሌዳ ቁጥር 3-77104 የሆነ ተሽከርካሪ ሙሉ ውድመት የደረሰበት ሲሆን የኢንሹራንስ ኩባንያዎች በሚከተሉት የአሰራር ደንብ መሰረት ቅሪት አካል ከሌሎች የመኪና ቅሪት አካሎች ጋር ተቀላቅሎ በጨረታ የሚሸጥ እንጂ ጉዳት እንዳልደረሰበት ተቆጥሮ ሊብሬና ክሊራንስ ታይቶ የሚሸጥ ባለመሆኑ ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ቅሪት አካል የሚመለከቱ ሰነዶችና ክሊራንስ ለመረከብ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክሯል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክርና ማስረጃን ከመረመረ በኋላ በሰጠው ውሳኔ መድን ሰጪ የሆነው ኢንሹራንስ ኩባንያ በንግድ ሕግ ቁጥር 683(1) የተጠበቀለትን የመዳረግ መብት ተግባራዊ ማድረግ የሚችለው በሶስተኛ ወገኖች ላይ እንጂ በደንበኛው ላይ ጭምር አይደለም በማለት ከመዳረግ መብት አኳያ ተጠሪ ያቀረበውን ዳኝነት ውድቅ አድርጓል፡፡ ቅሪት አካል እና ሊብሬ እንዲሁም ክሊራንስ ለመረከብ ያቀረበውን የዳኝነት ጥያቄንም በተመለከተ ተቀባይነት የለውም በማለት ክሱን ውድቅ አድርጎ ለአመልካች የወጪ ዝርዝር የማቅረብ መብት ጠብቋል፡፡

የአሁን ተጠሪ ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ ቅሪት የሚመለከቱ ሰነዶችን ለመረከብ ያቀረበው የዳኝነት ጥያቄ ውድቅ በመደረጉ እንዲሁም ለአመልካች የወጪ ዝርዝር የማቅረብ መብት መጠበቁን በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የይግባኝ አቤቱታ አቅርቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም የአሁን ተጠሪ ከተሽከርካሪው ቅሪት አካል ጋር የተያያዙ ሰነዶችን ለመረከብ ያቀረበው ዳኝነት ጥያቄ ውድቅ የመደረጉንና ለአሁን አመልካች ወጪ እና ኪሳራ የመወሰኑን አግባብነት ለማጣራት በሚል ይግባኙ ያስቀርባል በማለት ግራቀኙን ከአከራከረ በኃላ ወጪና ኪሳራ ለተጠሪ መጠበቁ በአግባቡ ነው በማለት ወስኗል፡፡ ከሰነዶቹ ጋር ተያይዞ የተነሳውን ክርክር በተመለከተ ተጠሪ ቅሪት

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

አካሉን ለመሸጥ ሊብሬ እና ክሊራንስ አያስፈልገውም ሊባል ስለማይችል አመልካች የተጠቀሱትን ሰነዶች ለተጠሪ ሊያስረክብ ይገባል በማለት የከፍተኛ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታም የቀረበው ይህንኑ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች ህዳር 23/2015 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያለውን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሶ በዚህ ችሎት እንዲታረምለት ጠይቋል፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮ የአመልካች ተሽከርካሪ ጠቅላላ ውድመት ደርሶበታል ተብሎ የመኪናው ዋጋ ተከፍሎ እያለ መኪናውን ከእዳ ነፃ አድርገህ ሰነዱን ለተጠሪ አስረክብ የተባለበት አግባብ በዚህ ችሎት ቀርቦ እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት ጠቅለል ባለ መልኩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

በዚህም መሰረት ግራ ቀኙን በዋነኛነት እያከራከረ ያለው ጉዳይ አመልካች ጉዳት የደረሰበትን ተሽከርካሪ የሚመለከት ክሊራንስ እና ሊብሬ እንዲያስረክብ መወሰኑ ነው፡፡ ይህንኑ ነጥብ አስመልክቶ የአመልካች መከራከሪያ ተሽከርካሪው ጠቅላላ ውድመት ደርሶበት ካሳ የተከፈለበት በመሆኑ እና በተለመደው አሰራር ተጠሪ የተሽከርካሪውን ቅሪት አካል ተረክቦ ከሌሎች ቅሪት አካሎች ጋር በማድረግ በጨረታ መሸጥ የሚችል በመሆኑ ሰነዶቹ አስፈላጊ አይደሉም፣ ሰነዶቹም ቢሆኑ በአደጋው ወቅት መጥፋቸውን አሳውቄ እያለሁ እና በተናጠል ክሊራንስ ማውጣት እንደማይቻል ተጠሪ እያወቀ ሆነ ብሎ አመልካችን ተጨማሪ ወጪ ለማስወጣት ከቅን ልቦና ተቃራኒ በሆነ መልኩ ክስ ያቀረበው ነው፣ ተሽከርካሪው ውድመት እንደደረሰበት የማሳወቅ ግዴታም የባለንብረቱ በመሆኑ የቀረበው ክርክር ተገቢነት የለውም የሚል ይዘት ያለው ነው፡፡ የተጠሪ መከራከሪያ ደግሞ ቅሪት አካሉን አስጠግኖ ለመጠቀምም ሆነ ባለበት ደረጃ በጨረታ ለመሸጥ እንዲሁም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ከተሽከርካሪዎች ዝርዝር ላይ ለማሰረዝ ክሊራንስ እና ሊብሬ አስፈላጊ ናቸው፣ አመልካች የተሽከርካሪውን ስመ ሀብት ተጠቅሞ ሌሎች ተግባራት እንዳያከናውን እንዲሁም ተሽከርካሪው የገባበት መንገድ ህጋዊነት ለማረጋገጥ ሰነዶቹ አስፈላጊ በመሆናቸው ከዚህ አንጻር የተሰጠው ውሳኔ ጉድለት የለበትም የሚል ነው፡፡

በመሰረቱ አንድ ሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሲሆን ተሽከርካሪውን በማስመዝገብ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር መያዝ እንዳለበት እንዲሁም ተሽከርካሪው ጨርሶ ከመንገድ ሲወጣ ወይንም አገልግሎት በማይሰጥበት ጊዜም ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ ተሽከርካሪውን ከተሽከርካሪ ዝርዝር ላይ እንዲሰርዝ የማሳወቅ ግዴታ ያለበት ስለመሆኑ ከተሽከርካሪ መለያ፣ መመርመሪያ እና መመዝገቢያ አዋጅ ቁጥር 681/2002 አንቀፅ 4፣9 እና 18 ድንጋጌዎች ይዘት ያስገነዝባሉ፡፡ በዚህ ረገድ ተጠሪ የተሽከርካሪው የባለቤትነት ደብተር ጠፍቷል የሚል መከራከሪያ በዚህ የሰበር ክርክር ወቅት የጠቀሰ ቢሆንም በእርግጥም የዚህ ዓይነት ክርክር በሥር ፍ/ቤት ቀርቦ የነበረ ስለመሆኑ የውሳኔው ግልባጭ አያሳይም፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ተጠሪ ሙሉ የጉዳት ካሳውን እስከከፍለ ድረስ ቅሪቱን አስጠግኖ ለመጠቀምም ሆነ በሌላ ግብይት ወደ ገንዘብ ለመቀየር የሚችል በመሆኑ ሰነዶቹን ለመጠየቅ አይችልም የሚባልበት የህግ መሰረት የለም፡፡ የተሽከርካሪው /ቅሪቱ/ ስመ ሀብት አግባብ ባለው ባለስልጣን መስሪያ ቤት ዘንድ ከተሽከርካሪ ዝርዝር እስካልተሰረ ድረስ ስም ሀብቱን መሰረት ተደርጎ ሊፈፀም የሚችልን ማናቸውም ህገ ወጥ ተግባራት ለመከላከል እንዲሁም ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተጠሪ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ላይ ሊቀርበ የሚችለውን ህጋዊ ተጠያቂነት ለማስቀረት ሲባል አመልካች ሰነዶቹን እንዲያስረክብ መባሉ የሚነቀፍ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ከዚህ አኳያ ይግባኝ ሰሚ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔ በአግባቡ ነው ከሚባል በቀር የሚነቀፍበት መሰረታዊ የህግ ስህተት ባለመኖሩ የአመልካች መከራከሪያ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩን ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/218634 ላይ ጥቅምት 02/2015 ዓ.ም የሥር ፍ/ቤቱን ውሳኔ በማሻሻል የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህግ ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በመዝገቡ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ዕ/ወ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !